# ህም!

፨
ጉድ!
ጊዜው እንደዘበት አስቀምጦን ንጉድ
አይናችን እያየ ልጅነትም እርፍድ
ጉድ!
ይገርማል አንችዬ
አ...ዬ!
በህይወት ጎርፍላይ አንቺም እኔም እሱም
ጭል...ጥ አልነው እልም
ላናጥነው ላይመለስ ዳግም
ህም!
አራት እንደ ዘበት
አለም እልም ጥፍት
የ'ድሜያችን ልቃቂት ከሙዳዩ ክትት
አቤ...ት!
የታል የትላንቱ
ሰማየ ሰማያት የነጎዱበቱ
እርገተ ስሜቱ
የተንሳፈፍንበት የዋሸንቱ ፉጨት
እህህ! አሄሄሄ! የከራሩ ቅኝት
የታለ ንዝረቱ?
ሁሉንም ጣጥለን የጠፋንበቱ
ያሰማችን ዜማ ኩኩ መለኮቴ
ኧረ ተይኝ እቴ!
ህም!
ጉድ!
መቼስ ምን ይደረግ
ትዝታ ስንቅ ሆኖ ነፍሳችን ሳትፈልግ
እኔም አንቺም እሱም ሁላችንም ጥርግ!
ጊዜም እንደዘበት አስቀምጦን ንጉድ
አይናችን እያየ ልጅነትም እርፍድ
ፕ!
አራት አመት ስልቅጥ
አንጎላችን ብጥብጥ
ጉንጫችንም ምጥጥ
ቀለም አጥበርብሮን
ፊደሉን ፈድለን
ቀመሩን ቀምረን
ወረቀት ወቅረን
ካመል አመል ነስቶን
ንጭንጭ ንዝንዝ አርጎን
አምና ካቻምናውም ጣጥሎን ነጎደ
ልጅነት ታጠበ እድሜም ረፈደ
ግንባርም ታረሰ ጢምም ተገመደ
እሳት አፍላው ጊዜ ረምጦ አመደ
አዲስ ሌላ ህይወት ጉልቻ ተጣደ

ይገርማል አንችዬ
አዬ ጉድ አዬ
ጊዜም እንደዘበት አስቀምጠን ንጉድ!
ጉድ!
፨፨፨፨፨፨
መስፍን አሸብር